# መግለጫ

# የሴት ልጆችን መግረዝ በመቃወም የወጣ

## ይህ መግለጫ ለምን አስፈለገ?

ይህን መግለጫ ወደ ውጭ ኣገር ይዘዉት መሄድ ይችላሉ። ቤተ ሰቦቻቸውንም ማሳየትም ይችላሉ። በዚሁ መሰረት የሴት ልጆች መግረዝ በሆላንድ በሕግ የሚያስቀጣ መሆኑን ሊያስረዱ ይችላሉ። ሴት ልጅዎን ካስገረዙ እርስዎ በወህኒቤት ሊገቡ እንደሚችሉ ያብራራሉ።

በየግዜው ወደ ውጭ ኣገር በሚሄዱበት ጊዜ ይህንን መግለጫ እንዳይረሱት ከጉዞ መስረጃዎችዎ (ከፓስፖርትዎ) ጋር ያስቀምጡ።

## ሴት ልጅን መግረዝ በሕግ ያስቀጣል።

**የሴት ልጅ ግረዘት በሰው ኣካል የሚፈጸም ከባድ በደል ስለሆነ በሕግ ያስቀጣል። ሴት ልጆችን መግረዝ የልጆችንና የሴቶችን ሰብኣዊ መብት መግፈፍ ነው። በሆላንድ ማነኛውም ዓይነት የሴቶች ግርዛት ብሕግ የተከለከለ ነው። ይህ ሕግ ለማነኛው በሆላንድ ኣገር የሚኖር ሰው፥ ቋሚ የመኖርያ ፍቃድ ባይኖረውም ይመለከትዋል።**

በሆላንድ የሴት ልጅ ግርዛት እንደ የልጅ በደል ተወስዶ ያስቀጣል። ይህ የግርዛት ወንጀል እስከ 12 ኣመት የሚደረስ እስራት ያስከትላል። የመግረዝ ወንጀሉ በወላጆች ከተደረገ ከፍ ያለ ቅጣት ያስከትላል (በሆላንድ መቅጫ ሕግ ኣንቀጽ 300 እስከ 304)

## ሴት ልጆችን መግረዝ በጣም ጎጂ ልማድ ነው።

**ሴት ልጆችን መግረዝ በጤንነታቸው ላይ ከባድ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። በሚገረዙበት ግዜ፥ ብዙ ደም ሊፈሳቸው ይችላል። በዚህ ምክንያት ወደ ኣደገኛ በሽታ ወይም ሞት ሊዳረጉ ይችላሉ።**

ከተገረዙም በኋላም ብዙ ስቃይ ይደርስባቸዋል። ለምሣሌ፣ በሚሸኑበትና የወር ኣበባ የሚያዩበት ግዜ፥ , በእርግዝና በወሊድ ጊዜ ከባድ ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል። ከጊዜ በኋላም የመንፈስ ጭንቀት ልያመጣባቸው ይችላል።በእነዚህ ሁሉ ምክንያት ብዙ ሴቶች ብሂወታቸው ሙሉ ስቃይና የጤና ችግር ሊገጥማቸው ይችላል።

በልጆቻቸው ላይ የመግረዝ ተግባርን የፈፀሙ ወላጆች ፣ ድርጊቱን በሌላ ሃገር መፈፀማቸው ከተረጋገጠ፣ በኔዘርላንድ ህግ መሰረት ተገቢውን ቅጣት እንዲቀበሉ ይደረጋል።

ወላጆችም ሆኑ ሌላ ወገን በሴቶች ላይ የግርዘት ተግባር እንዲፈፀም ካደረጉት ወይም በሌላ ሃገር እንዲካሄድ ካቀናጁ፣ በኔዘርላንድ ህግ መሰረት ይቀጣሉ።'

ወላጆች ይህንን የግርዘት ድርጊት በልጃቸው ላይ መፈፀማቸው ተረጋግጦ የተፈረደባቸው ከሆኑና ወይም በሌላ አካል እንዲፈፀም ካደረጉት፣ የሆላንድ ፓስፖርት ከሌላቸው በኔዘርላንድ ውስጥ መኖሪያ ፈቃድ የማግገኘት መብታቸውን ሊያጡ ይችላሉ።

ይህ መግለጫ የሴት ልጅ ግርዛት በመቃወም የወጣ ሲሆን፣ ኣላማው ልጃገረዶች በኣካልዊና በኣእምሮኣዊ ጤነኛ ሆኖው እንድያድጉ ነው።

ከኣክብሮት ጋር,

የጤና፡ የማሕበራዊ ድሕነት እና ስፖርት ሚኒስተር፥
ሑጎ ደ ዮንገ

የሕግ ጥበቃ ሚኒስተር፡ ሳንደር ዴከር

## ጥያቄ ኣለዎት?

ስለ ሴት ልጅች ግርዛትና ስለዚህ መግለቻ ትጸግሟል? ጥያቄ ካለዎት፣ በማነኛውም ጊዜ ወደ ሚመለከተው ኣማካሪ ጽህፈት ቤት ወይም ወደ ማዛጋጃ ቤቶች ጤና (CGD) ኣገልግሎት በመሄድ ከሃኪም ወይም ከነርስ ጋር ቀጥሮ መያዝ ይችላሉ። ለተጨማሪ ማስረጃ፣ በዚህ ድህረ ገጾች እንግሊዘኛ ቋንቋ መጎብኘት ይችላሉ።
www.meisjesbesnijdenis.nl እና
www.tegenvrouwenbesnijdenis.nl

ይህ መግለጫ የወጣው ፤

በጤና ጥበቃና ስፖርት ሚኒስቴርና

በደህንነትና የፍትህ ሚኒስቴር ነው።

ሰኔ 2019

*Amhaars*

# የሴት ልጆችን መግረዝ በመቃወም የወጣ መግለጫ

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ድርጅቶች የተደገፈ ነው፣

Angela Bransen
ActiZ ወጣቶች

Astrid Nielen
AJN የወጣቶች ሐኪም ኔደርላንድ

dhr. A. Ware
የሶማል ፌደራስዮን ማህበር በሆላንድ

Annemieke van der Bas
የሚስጥራዊ ሐኪሞች ማሕበር የሕጻናት በደል እና የቤት ውስጥ ጥቃት (VVAK)

mw. Y.A.J.M. Dabekausen
የዳች የማህጸን ባለሞያዎች ህብረተሰብ

dhr. H.A.M. Backx
የዳች የመዘጋጃቤት የጤና ኣገልግሎት ማህበር በሆላንድ

René Héman
የዳች የንጉሳዊ ቤተሰብ የህክምና ማህበር

Mieke Beentjes
የሆላንድ የንጉሳዊ ቤተሰብ Midwives ድርጅት

mw. drs. P. Heijdenrijk
ፋሮስ፡ የሞያውያን ማእከል ጤናዊ ልዩነት

mw. drs. F. Z. Özgümüş
የስደተኞች ድርጅት በሆላንድ

የዎላጆች ፊርማ

የሴት ልጆችን መግረዝ በመቃወም የወጣ መግለጫ